ፓኖራማ ቁጥር 55

የትዝብት አድማስ

ታህሣሥ 10 ቀን 2001 ዓም

<u>የኢሕአፓ ተጠያቂነትና ኃላፊነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነው።</u>

እንደማነኛውም ለሕዝብ ነፃነትና መብት እንደሚታገል የፖለቲካ ፓርቲ ሁሉ፥ ኢሕአፓም የመጀመሪያው፥ተጠያቂነት፥ ኃላፊነቱና ግዴታው ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንጅ ለማንም ወገንና ኃይል እንዳልሆነ፥የረዥም ጊዜ የትግል ገድሉና ታሪኩ ህያው ምስክሮቹ ናቸው። ይህንንም እንኳን የሚታገልለት ሕዝብ ቀርቶ፥ባለንጣዎቹም ሳይቀሩ አሌ ሊሉት የሚችሉት ክስተት አይደለም።መንግሥቱ ኃይለማርያምም ይሁን መለስ ዜናዊ እንኳን ሊያስተባብሉት አልቻሉም/አይችሉምም።ይህንን የፓርቲ አይበገሬነት፥ እንደ ግትርነት የሚቆጥሩት እንደማይጠፉ ብንረዳም፥ እንዳላችሁት ይሁንላችሁ ከማለት በስተቀር፥ ለእነርሱ ማስተባበያ ለማቅረብ የምንቸገር አንሆንም። " ሥራው ለሰሪው እሾህ ለአጣሪው" ብለን በመተው ወያኔን ለመፋለም የምናደርገውን የሞት ሽረት ትግል ከማፋፋም በስተቀር ሌላ አጀንዳ እንደሌለን የሚያውቀን ያውቀናል። ለማወቅ የማይሻው ግን ሊያውቅ አይፈልግም።ይህ ደግሞ እኛን የሚያስጨንቀን አይሆንም።

አልፎ አልፎ በተደጋጋሚ ያለመታከት ከአንዳንድ ወገኖች የሚሰማውን በምናልባታዊ ብልጭታ ላይ የተመሠረተ ዝባንዝንኪ ከቁም ነገር ቆጥሮ በርሱ ላይ ጊዜ ለማጥፋት ሳይሆን፥ለምንታገልለት ምልዐተ-ሕዝብ ካለን ተጠያቂነት በመነሳት፥ቁጥራቸው ከአንድ እጅ ጣቶች የማይበልጡ ክፍሎች የሚነዙትን የውሸንፍር ጭጋግ ለመግፈፍ ብቻ ስንል ለኅብረተሰቡ ግልፅ ሊሆኑ የሚገባቸውን ጉዳዮች ግን ከመግለፅ አንታክትም። ፓርቲው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃ አውጭና መብትንም አስጠባቂ ድርጅት እንደመሆኑ፥ በአመለካከት፥ በአስተሳሰብ፥ በነባቢትና በድርጊት ኢትዮጵያዊ ከመሆን በቀር ሌላ መለያ ሊኖረው አይችልም። ስለሆነም፥ጠላትን ለመቋቋም፥ለመከታተልና ለማጥቃት ከሚደረገው ሂደት ውጭ፥ ከኅብረተሰቡ ጋር የምናደርገው ግንኙነትም ይሁን የምንሰራው ተግባርና የምናወጣቸው ጽሁፎች ሁሉ ግልፅነትንና ቀጥተኛነትን የተላበሱ ናቸው። የራሳችንና ታዋቂ የሆነው ልሳናችን <u>**ዲሞክራሲያና**</u> **ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ የድርጅቱን**

መግለጫዎች፥ፖሊሲዎች፥ዘገባዎች፥አዋጆች፥ ማስታወቂያዎች ወዘተ.. ለሕዝብ የምናሳውቅባቸው መድረኮችና ልሳኖቻችን ናቸው። ስለሆኑም፥በእነርሱ ላይ በሚወጡት ማነኛዎቹም ጽሁፎች ሁሉ ፓርቲው ተጠያቂና ኃላፊነት ይኖረዋል። በሌሎች ሰፈዶችና መሽረፊቶች ስለ ሚራገቡት ሁሉ ፓርቲውን አይመለከተውም። ሽሮው ያረረበት ሁሉ፥ ያሳረረብኝ ኢሕአፓ ይሆናል ብሎ ከሚጨነቅ፥የምድጃውን ባኅርይ ቢያስተካክል ይሻለዋል ነው።

ዛሬ በዘመነ ቴክኒዮሎጂ ዕድገት፥ምጥቀትና ስፋት የተነሳ፥ የመገናኛ ብዙኃን አገልግሎትና ስርጭት ከአድማስ እስከ አድማስ ኅብረተሰቡ በሚያስደንቅ ፍጥነት ይገለገልበታል። ይህ ደግሞ፥የሰውን ልጅ አገናኝቶታል፥ አቀራርቦታልም። ይህ ክስተትና ሂደት የሚደገፍና የሚወደድ ነው።ይህንም የሥልጣኔ ዕድገት ማንም በግል ባለቤትነት ሊወስነውና ሊቆጣጠረው አልቻለም። ሊወስነውና ሊቆጣጠረውም ከቶ አይገባም። ሊቆጣጠር ቢከጅልም ፈጽሞ የሚሳካለት አይሆንም። ዛሬ የኢትዮጵያ ኅብረተስብ በውጭም ይሁን በሀገር ቤት ይህንን የቴክኒዮሎጂና የሳይንስ ዕድገት ዕድል በብዛት እየተጠቀመ ይገለገልበታል። አብሶማ በመላው ዓለም የተሰራጨው የዲያስፖራው ኅብረተሰብ ዓይነተኛ የመገናኛ መድረኩ ከአደረገው ሰንበትበት ብሏል። ይህ መድረክ፥ ወያኔን በመቃወም ሂደት ውስጥ ዓይነተኛ ሚና ከመጫወቱም አልፎ ተርፎ፥ የዓላማ አንድነት ያላቸውን ወገኖች ለማቀራረብ የሚያደርገው ተግባር በቀላሉ የሚገመት አልሆነም።የዚህም አንድ አካልና አምሳል ከሆኑት ውስጥ፥የድረ ገፅ መድረኮች፥ የፓል ቶክ ውይይቶች፥ የኢሜይል ግንኙነቶችና ራዲዮም ጭምር፥ በዋናነት ከሚጠቀሱት ጥቂቶቹ ናቸው። እነኚህ 98 በመቶ ህዝባችንን የሚመለከቱ እንዳይደሉም መጠቅስ ያለበት ነው።

በአሁኑ ወቅት፥የተያዘው የተረዘዘው ሁሉ በየስርቻው እንደ እንጉዳይ የፓል ቶክ መድረኮችን በመክፈት የሃያ አራት ስዓታት አገልገሎት ይጠቀማል። ይህ ደግሞ የሚከፋ አይደለም። እንዲያውም በአግባቡ መጠቀም ከተቻለ፥ መሠረታዊና ገንቢ የሆነ አገልግሎት ከመስጠት በስተቀር፥ አሉታዊ ነገር አይኖረውም። ለማነኛውም ጽሁፍም ሆነ ንግግር ተጠያቂና ኃላፊነት የሚኖረው ግን ፓልቶኩንና መድረኮችን በባለቤትነት ይዞ የሚቆጣጠራቸው ክፍል ነው የሚሆነው። ሌላው ክፍል ባልገባበት፥ ባልተቆጣጠረውና በማያዝበት መድረክ ተጠያቂነትም ሆነ ኃላፊነት፥ ወይም ግዴታና መብት ሊኖረው አይችልም። ይህ ደግሞ የመብትና ግዳታ የተጠያቂነትና የኃላፊነት ትምህርት ሀ ሁ ስለሆነ ብዙ ትንታኔና ስንክሳር የሚያሻው አይሆንም።የአንዱን ባለቤትነትና ኃላፊነት በቀጥታም ይሁን በአንደምታ ወደ ሌላው መላከክ፥ “ ላም ባለዋለበት ኩበት ለቀማ ”

ነው የሚሆነው:: ኢሕአፓን የሚጠሉትና የሚፈሩት ሁሉ÷ ፓርቲውን ያጥላሉትና ያሳጡት እንዲሁም ትግሉንም የሚያሰናክሉት እየመሰላቸው በከንቱ ሲማስኑ እንገነዘባለን:: ሁሉንም መጥፎ ሥራ ሁሉ ኢሕአፓ ነው የሚሰራው ብለው ስለሚገምቱ÷ ይህንን ግምታቸውን ለማሳመን ረዥም ምዕራፍ በመሄድ ይባዝናሉ::በየድረ ገፆቹና በየመድረኮቹ የሚፃፉትን ጽሁፎች ሁሉ ኢሕአፓ ነው የሚጽፈው ይላሉ:: የብዙዎች ፓልቶኮቹንም መድረኮች በሙሉ ፓርቲው የሚያሽከረክራቸው÷÷ የሚቆጣጠራቸውና አቅጣጫ የሚሰጣቸው እያስመሰሉ የአሉባልታ መርዝ ይረጫሉ÷ ያስረጫሉ:: ይህ ደግሞ ከፍርሃትና ከጥላቻ የመነጨ ከፉ ባኅርይና አደገኛ የተፈጥሮ ጠባይ ነው::ተደጋግሞ እንደተገለፀው÷ ፍርሃትና ጥላቻ ከተዳበሉ ÷ በምክርም ሆነ በተግሳፅ የሚድኑ አይደሉም:: በዚህ መርዘኛ የሥነ አዕምሮ ደዌ የተለከፉ ክፍሎች ሁሉ እናጠፋዋለን ያሉትን ሳይሆን በመጨረሻ የሚያጠፉት እነርሱን እራሳቸውን ለመሆኑ የኢትየዮጵያ ይትብሃል መዝግቦታል:: ለዚህም ነው የህገራችን ሕዝብ :-

"አትዋል ይዋሉብህ÷ ክፉውን አትምከር÷ እነርሱ ይምከሩ÷
በቆፈሩት ጉድጓድ ሳይገቡም አይቀሩ::

"ክፉ ሰሩኝ ብለህ ክፉ አትስራባቸው÷ አትበቀላቸው÷
ይመለሱ ይሆናል ህሌና ካላቸው÷ ፀፀት ከገባቸው::"

እያለ የሚመክረው÷ የሚያስተምረው÷ የሚታዘበውም::

ሁሉንም ነገር ኢሕአፓ ይሰረዋል÷ ያደርገዋል ይጽፈዋል÷ ይቆጣጠረዋል÷ ያጠፋዋል÷ ያበላሻዋል ወዘተ..ብሎ ማለት÷ በመሠረቱ ሁለት ዐቢይ ስህተቶች እንደመፈፀም ይቆጠራል:: አንደኛው÷ፓርቲውን÷ የሌለውን ሁለንተናዊ ኃይልና ሥልጣን እንደመስጠት ነው:: ይህ ደግሞ÷የሃይማኖት ሰዎች እንደሚያምኑበት መለኮታዊ ባኅርይና ኃይል እንዳለው አድርጎ መስጠት ይሆናል:: "አምላክ በቦታና በጊዜ የሚወስን አይደለም" ብለው የሃይማኖት መሪዎች ያስተምራሉ:: በዚህ እምነት መሠረት÷ በሁሉም ቦታና ወቅት ሊገኝ የሚችል መለኮት እንጅ፤ ሰዎች የፈጠሩት የኢሕአፓ ባኅርይና ሰብዕና ከቶ ሊሆን አይችልም:: ሁለተኛው ደግሞ÷ ሁሉንም ሰው ኢሕአፓ ይቆጣጠረዋል÷ያዘዋል÷ ይነዳዋል÷ ብሎም በየመድረኮቹ የሚወጡትንና በሁሉም ቦታዎች የሚጻፉትን ጽሁፎች ሁሉ÷ የኢሕአፓ እጅ አለበት ወዘተ ብሎ ማሰብ÷ የሌላውን ሰው÷ ስብዕና መዳፈር ነው:: የሌላውን ሰው አዕምሮ ብቃትና ብስለትን መሳደብና መናቅ ይሆናል:: ይህ አመለካከት ደግሞ÷በሃያ አንደኛው ምዕተ ዓመት እኖራለሁ በሚል ግለሰብም ይሁን ማኅበረሰብ በኩል ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችል አይሆንም:: በዕርግጥ በድንጋይ ዘመን መኖርን እንፈልጋልን

ካልተባለ በስተቀር!

ግራም ነፈሰ ቀኝ፥ ፓርቲው በርግጠኝነት አምኖ የተቀበላቸውን መተከላዊ አቋሞቹንና የትግል መርኅዎች፥ ለሕዝቡ የገባቸውን ሀገራዊ ቃልኪ ዳኖችና ብሔራዊ ራዕይ እውን እንዲሆኑ በፅናት ከመታገለ ፍንክች አይልም፡፡ ባገኘው መድረክና የትግል ሜዳም የመጀመሪያ ዒላማ ያደረገውን ዘረኛውን ሥርዓትና አራማጆቹን ከመፋለም ሌላ የተለየ አጀንዳና ፕሮግራም የለውም፡፡ ይህንን ከማድረግ ደግሞ የማንም ጥላቻና ፍራቻ አይበግረውም፡፡ ወያኔ በሚወገዝበትና በሚጠቃበት መድረክ ሁሉ ኢሕአፓ በአካልም በመንፈስም አለ / ይኖራልም፡፡ በአሉባልታውና በአስመሳዮች የጨረባ ተዝካር መድረክ ይህ የሕዝብ ድርጅት ድርሽም አይልም፡፡ ትግላችን ፀረ ወያኔ ነው፡፡ ትኩረታችን በዚህ የሕዝብ ጠላት ላይ ነው፡፡ በጎድን ርዕሶችና አሳሳች ተልዕኮዎች አንጠመድም፡፡ ለሕዘብ ያለንም ጥሪ በፀረ ወያኔ ትግሉ ላይ በጋራ እናተኩር የሚል ብቻ ነው፡፡